# መምህሩ ተሰዋ!



ሕይወቱን ከፈለ ለነፃነት ዋጋ፤
ነፃነት ወይስ ሞት በማለት ተሰዋ!
ሰማይ ደም መሰለ ፣
ሕዝባችን አዘነ፣
መሬትም አትዞርም፣
ጅረቶች አይወርዱም።
ወፎች እርጭ አሉ፤
አይር መተንፈሱን ፍጥረታት አቆሙ፤
መምህሩ የኔሰው ተሰዋን ሲሰሙ።
አልሞተም የኔሰው ፣
ማነው ሞተ ያለው?
በዋካ ከተማ ሲያስተምር አየነው።
ነፃነት ለጠማው፣
ሲያጠጣ አገኘነው።
ነፃነት ተጠምቶ መኖር ከተቻለ፣
ትዎድሮስ ሽጉጡን አይጠጣም፣ ነበረ።
የኔሰው ገብርዬ መስዕዋት ባልሆነ፣
በሃገራችን ምድር ፍትሕ በነበረ።
ኢንግሊዝ ጅግና ነው ጅግና አከበረ፣
ለመይሣው ሬሣ ሰላምታውን ሰጠ።
ወያኔ ርካሽ ነው በጣም የረከሰ፤
ጅግናውን፣ የኔሰው፣ ማራከስ ጀመረ።
ጥንትም አውቀነዋል፣ አዲስ ነገር የለም፤
ከዕባብ ዕንቁላል፣ ዕርግብ አንጠብቅም።

ታደለ መኩሪያ
tadele@shaw.ca